## ከቶ አይቀርም ሞቱ

ከቶ አይቀርም ሞቱ
ምን ቢሰነብቱ
ምንም ቢታክቱቱ

መፍረሱ እንደሁ አይቀር ሁሉ መበስበሱ
የተካበው ሁሉ....አይቀር መደርመሱ

ትናጋው ይዘጋል
ምላሱ ይተላል
ትንፋሹ ይረጋል
ጉሮሮው ይገግል

አይኑ ይቆለፋል
ከንፈሩ ይከስላል
ጀማቱ ይረግባል

እጆቹ ተጣጥፈው
እግሮቹም ደርቀው

ቆዳው ደርቆ ነጥቶ
የነፍሱ ድር ላልቶ

ከቶ አይቀርም ሞቱ
ይብላልኝ ለናቱ
ይብላልኝ ላባቱ

አባ ጭሌው ጀግና
ሳተናው ጀቢራው ይበሰብስና....

ይሰባበርና ተንዶ ይወድቃል
ከህያዋን ምድር እጣው ይቀረጣል
እቁቡ ይፈርሳል..

ሽቶው ይከረፋል
ዝባዱ ይገማል
መርዶው ይነገራል

እሬሳ ይሆናል
እስከሬኑ ጀግና በሳጥን ይገባል

እግሮቹ እንዳልሮጡ
ወደ ፈቀደበት እንዳልፈረጠጡ

እንደ ንስር በርሮ....
እንዳንበሳ አግስቶ....ሁሉን አሸብሮ

ፍጥረት እንዳልፈራው
ክብሩ እስከሰማይ ይደርስ የመሰለዉ

ከንቱ የተሞኘው
በትእቢት አንቀልባ እራሱን ያዘለው

ጉዱ ፈላ ዛሬ
ሲደርስ የሱ ጥሪ

እንግዳው መጣና ....
በር ሳይቆረቁር በርግዶ ገባና
እንደ ነሃሴ ጎርፍ አጥለቀለቀና

ነጠቀው ውበቱን
አረከሰው ኩሉን
ደፈረው ድንግሉን

ሰረቀው ....ጀግናውን ከገዛ እጁ ለፊው
መቼ ፋታ ሰጠው....
ወደ ላይ አወጣው
ወደምድር ጣለው....
ካፈር ጋር ለውሶ አፈር አደረገው....

ነፍሱ ነፍሳን አጣች
አድባሩ ደንግጣ .....ሮጣ ከነፈች
ጀንበሩም ጠለቀች

ከዳችው ትንፋሹ....ከሞት ጋር ተዳርታ
ምንዝር ገባችና....ከስጋው ተጣልታ

ቁልቁል እያየቸው ፈረጠጠች ጠፋች
መቼ አራብው ቆመች
መች አራብው ተኛች

ከቶ አይቀርም ሞቱ
ምን ቢሰነብቱ
ምንም ቢታክቱ
ይብላልኝ ለናቱ
ይብላልኝ ላባቱ
ቆመው ለቀሩቱ......

ዘውዱ ሳህሉ
September 2007

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot****. You may contact Zewdu Sahlu  for comments at*** *zewdu_michael@yahoo.com*